- 22 -

ይህ ዓለም እስር ቤት ነው ወይስ ጀነት?

አየር ማረፊያ ውስጥ ነኝ። ተራዬን ለመጠበቅ በፍተሻ መስመሩ ሳጥን ውስጥ ቆሜያለሁ። እዚያው ቆሜ እያለሁ አንዲትን ትንሽ ልጅ ከእናቷ ጋር አየሁ። ልጅቷ ታለቅሳለች። እንደታመመች ታስታውቃለች። እናት ለልጇ መድሃኒት ለመስጠት ብላ እጇን ወደ ቦርሳዋ ሰደደች። የልጅቷ እንደዚያ መሰቃየት አሳዘነኝ። ወዲያውኑ ግን አንድ ነገር አሰላሰልኩ። በወጥመድ የተያዘ ሰው እያየሁ ያለሁ መሠለኝ። ይህች የዋህ ነፍስ ትታመምና ትሰቃይ ዘንድ በአንድ ዓለማዊ በሆነ አካል ውስጥ ታስራለች - በሰውነት ውስጥ።

ቀጥሎ ያስታወስኩት ነገር የአላህን መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሐዲሥ ነበር። እንዲህ የሚለውን "ይህች ዓለም ለአማኝ እስር ቤት ናት፤ ለከሀዲ ጀነት ናት።" (ኢማም ሙስሊም እንደዘገቡት)

ለመጀመርያ ጊዜ ሐዲሡን ከዚህ ቀደም ከምረዳው ለየት ባለ መልኩ ተረዳሁት። ብዙ ሰዎች ይህን ሐዲሥ ትከክል ባልሆነ መልኩ ሲተረጉሙትና ሲተነትኑት አያለሁ። ይህች ዓለም የተፈጠረችው አማኝ ላልሆኑት እንዲዝናኑባትና እንዲጨፍሩበት ነው። አማኞች ግን "ሐራም" እና "ሐላል" በሚል መመርያ እንደፈለጉ እንዳይሆኑ ታግደዋል። መዝናናትና መደሰት ከፈለጉ የመጨረሻውን ዓለም መጠበቅ ይኖርባቸዋል .. የሚል። ወይም ደግሞ ይህ ዓለም ለሙስሊሞች የመከራ ዓለም ነው፤ ለኢ-አማኞች ግን የፌሽታ።

በበኩሌ እንደዚያ አይመስለኝም። ሙሉ በሙሉ እንዲህ ነው ብዬ አልረዳም።

የሐዲሡን እውነታ በልጅቷ ውስጥ ሲተገበር እያየሁ ያለሁ መሠለኝ። በሌላ በኩል ደግሞ ይህች የታሠረችው ነፍስ ቦታዋ ይህ ሳይሆን ሌላ ዓለም ነው። ያ በሽታ፣ ሕመምና ስቃይ የሌለበት አገር ብዬ አሰብኩ።

ተቃራኒው ቢሆን ኖሮ ምን ሊከሠት ይችል ነበር? አንዲት ነፍስ ጀነት ውስጥ ነኝ ብላ ብታስብ ምን ትሆናለች? ከዚያ ውጭ ርቃ ሌላ ቦታ መሆን ትፈልጋለችን? ሌላ የተሻለ አካባቢ ታስባለችን? አታስብም። በፍጹም። መሆን የምትፈልገው እዚያው ነው። ለዚያች ነፍስ ጀነት እንደገባች ነው የሚሰማት። ከዚያ የተሻለ ቦታ ያለ አይመስላትም። ሌላ አታልምም። በያዘችው ነገር በቅቷታል፣ ባገኘችው ነገር ረክታለች። የዚያ ዓይነቱ ሁኔታ የኢ-አማኞች ነው። ሕይወታቸውና ደስታቸው ያ ዓለም ብቻ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል:-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ لَا يَرۡجُونَ لِقَآءَنَا وَرَضُواْ بِٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَٱطۡمَأَنُّواْ بِهَا وَٱلَّذِينَ هُمۡ عَنۡ ءَايَٰتِنَا غَٰفِلُونَ ﴾

«እነዚያ መገናኘታችንን የማይፈሩ፤ ቅርቢቱንም ሕይወት የወደዱ፤ በሷም የረኩ፤እነዚያም እነሱ ከአንቀፃቻችን ዘንጊዎች የኾኑ።» (ዩኑስ : 7)

ላላመኑ ነፍሶች፤ ይህ ሕመምና ችግር የበዛበት ጊዜያዊ ዓለም በርግጥም ጀነታቸው ነው። እነሱ እሱን ብቻ ነው የሚያውቁት። እስቲ አስቡት ይህ ወድቃችሁ የምትነሱበት፣ የምትደሙበት እና የምትሞቱበት ዓለም የምታውቁት ጀነት ብቻ ቢሆን ስቃዩ ምን ያህል እንደሆነ ልብ በሉ።

ግና ይህ ፈጽሞ ጀነት ሊሆን አይችልም። ጀነትም አይደለም።

ከዚህ የተሻለ ሌላ የጀነት ዓለም የለም፤ ሁሉንም ነገር የምናገኘው በዚሁ ዓለም ላይ ብቻ ነው ብሎ የሚያስብ ሰው ይህች ዓለም በአሉታዊ ጎኗ ስትነካካው ፍፁም እንዳልሆነች ሲገባው፣ ትዕግስት ማጣቱና ተስፋ መቁረጡ አይቀርም። በንዴት ላይ ንዴትን ይደርባል። በእጅጉም ይጎዳል። ምክንያቱም ይህ ዓለም ገነት ነው ብሎ አስቦ የነበረ ቢሆንም አልሆነምና። እንዲያ የሚያስቡት ከዚህ የበለጠ ሌላ ትልቅ ነገር እንዳለ አልተረዱም። ስለሆነም የሚፈልጉት ይኸንኑ ብቻ ነው። ለሱ ብቻ ነው የሚደከሙት። የትኛውም ጥረት፣ የትኛውም ችሎታ፣ የትኛውም ዕድል፣ የትኛውም ስጦታ ለነርሱ የተሠጠው በፈጠራቸው ፈጣሪ ነው። ያንንም ስጦታ የሚያውሉት ለዚህ ዓለም ስኬት ብቻ ነው። ግና የቱን ያህል ቢለፉም ከተግፈላቸው ነገር ውጭ የሚደርሣቸው ምንም ነገር የለም።

ነፍሣቸው የዓለማዊ ሥሪት ውጤት ከሆነው ገላ ጋር አጥብቃ ተሳስራለች። ያ ገላም ከዚህ የበለጠ ጀነት የለውም፤ ወደፊትም አይኖረውም ብለው ያስባሉ። ስለሆነም ትታው ልትሄድ አትሻም። የትኛውንም ዋጋ ከፍላ ከርሱ ጋር መኖርን ትመኛለች። ከዚህ እርሷ ጀነት ነው ብላ ከምታስበው ዓለም መውጣት ለሷ ከባድ ህመም ነው።ትልቅ ስቃይ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) የኢ - አማኒያንን አሟሟት ሲገልጽ ነፍስን ከሰውነት ውስጥ በኃይል መመንጨቅ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። እንዲህ በማለት-

﴿ وَٱلنَّٰزِعَٰتِ غَرۡقٗا ﴾

‹‹በኃይል አውጪዎች በሆኑት›› (አን-ናዚዓት : 1)

በኃይል መንጭቀው የሚያወጡት ይህች ነፍስ ይህን ዓለም መልቀቅ ስለማትፈልግ ነው። ምክንያቱም በአሁኑ ሕይወቷ ጀነት ውስጥ ያለች ያህል ምቾት ተሰምቷታልና። ከዚህ የበለጠ ሕይወት ያለ አይመስላትም።

የአማኝ ነፍስ ግን ሁኔታዋ ከዚህ ይለያል። አማኝ በጊዜያዊ እስር ቤት ውስጥ ነው- ጀነት ውስጥ አይደለም ያለው። እንዴት ከተባለ እስር ቤት ምን እንደሆነ ማስታወስ ያስፈልጋል።

እስር ቤት አንድ ሰው ተይዞ የሚታሰርበት ቦታ ነው። ከቤተሰቡና ከቤቱ ርቆ ታግዶ የሚቆይበት ነው። የተመኘውን ማድረግ ቢፈልግ አይቻለውም። መውጣት ቢፈልግ ሊፈቀድለትም። ቁሳዊው ዓለም ለአማኝ እስር ቤት ነው። ምክንያቱ ደግሞ ይህ ዓለም ለአማኙ የስቃይ ዓለም ስለሆነ አይደለም። ምክንያቱም ያች ውድ ነፍስ የተሻለ ዓለም ስለሚገባት ነው። ከሚገባት ቤቷ መሆን አለባት። ወደ እውነተኛው ጀነቷ። ይህ ዓለም የቱንም ያህል በተድላና ጸጋ ቢሞላም ወደፊት ከሚጠብቀው ዓለም ጋር ሲነፃፀር ለአማኝ እስር ቤቱ ነው። ይህች ነፍስ ልትተሳሰር የሚገባው ከአምላኳ እና ከእውነተኛ ጀነቱ ጋር ነው። እዚያ መሆንን ትፈልጋለች። ግና ይህ ዓለም ይህችን ነፍስ ወደኋላ ይመልሳታል። ከአምላኳ ጋር እንዳትገናኝ ግርዶ ሆኖባታል። እስር ቤት ነው። የአማኝ ልብ በጀነት ውስጥ እንዳለች ሆና ቢሰማትም ከዚያ ባሻገርም ትመኛለች። ገነትን ትናፍቃለች። የጥንት ቤቷ ነውና። ግና ጊዜው እስኪደርስ ድረስ ይህች ነፍስ ሰውነት በሚባል ክልል ውስጥ እንድትቆይ ተደርጋለች። ወደቤቷ ለመሄድ ትሿድ" የሚለውን የአምላኳን ፈቃድ ትጠባበቃለች። የአማኝ ነፍስ በሰውነት ውስጥ የታሠረች አይደለችም። ፍርዱ ሲያልቅ ምርኮኛው ወደ ቤቱ እንዲሄድ ይነገረዋል። ያኔ ነፃ ይወጣል። ለዚህም ነው አላህ (ሱ.ወ.) የአማኝን ሞት በተለየ መልኩ የሚገልጸው። እንዲህ በማለት:-

﴿وَٱلنَّٰشِطَٰتِ نَشۡطٗا﴾

‹‹በቀስታ መምዘዝንም መዛዦች በሆኑት›› (አን-ናዚዓት: 2)

አማኝ ነፍስ ግን ልክ ፀጉር ከቅቤ ውስጥ እንደሚመዘዘው ሁሉ ቀስ ተብላ እንድትወጣ ትደረጋለች። "የእስር ፍርዷ" ያኔ ያበቃል። ዱንያ እስር ቤቱ ነበረችና። አሁን ወደቤት የመሄጃ ጊዜው ነው። ወደ ቀደመ ቤቱ - ወደ ጀነቱ። እሳቤውና እምነቱ እንደ ከሀዲ አልነበረም። ምርጡ ዓለም ይህ ሳይሆን ያኛው ነው- ቀጣዩ ዓለም፣ ጀነት።

ለዚህ ሁሉ የተሟላ ማነፃፀሪያ ይሆንልን ዘንድ ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በላይ የተሻለ ንግግር አላገኘለትም " በርግጥም ይህ ዓለም ለአማኝ እስር ቤት፣ ለከሀዲ ደግሞ ጀነት ነው።" እኛ ሁላችንም በተመሳሳይ ጠሪ አማካይነት እንጠራለን። ጥያቄው የሚሆነው እኛ ኑሯችንን በመኖር ላይ እያለን ጥሪው በሚመጣበት ጊዜ ወደ እስር ቤት ሊወስደን ነው ወይስ ከእስር ቤት አውጥቶ ወደቀደመው ቤታችን ወደ ጀነት ሊመልሰንና ከእስር ቤት ነፃ ሊያወጣን?

- 23 -

ከፈጣሪ ጋር የሚኖር ግንኙነት

ሶላት - የተረሳው የሕይወት ዓላማ

የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ በርካታ ጉዞዎችን አድርጓል። ግና ከአንድ ሰው በስተቀር አንድም ሰው ያልተጓዘው አንድ ምርጥ ጉዞ አለ።

አዎ ከአንድ ሰው በስተቀር ያንን ጉዞ ማንም አልተጓዘውም።

በዚያ መጓጓጥ ማንም አልተጓጓዘም፤ በዚያ መንገድ አንዲትም ነፍስ አልሄደችም። ያን ቦታ አንድም ፍጡር ረግጦት አያውቅም። ያ ጉዞ የአንድ ሰው ጉዞ ነበር። መለኮታዊውን ዓለም ለማየት በተደረገ ግብጥ የተደረገ ጉዞ።

ያ ጉዞ የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) ጉዞ ነበር። ወደ ላዕላዩ ዓለም ያደረጉት ጉዞ።

ጉዞው "ኢስራእ" እና "ሚዕራጅ" በመባል ይታወቃል። በዚያ ጉዞ አላህ (ሱ.ወ.) ተወዳጁን ነቢይ ወደ ሰባተኛው ሰማይ ወሰዳቸው። ታላቁ ጂብሪል እንኳን እዚያ ቦታ ፈጽሞ ረግጦ አያውቅም። ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) በምድር ላይ ባላቸው ነቢያዊ ተልዕኮ መልዕክት የሚደርሳቸው በመልኣኩ ጂብሪል(ዐ.ሰ.) በኩል ነበር። ከመልዕክቶች ሁሉ ግን ምድር ላይ እያሉ ሳይሆን ወደ ሰማይ ወጥተው የተቀበሉት አንድ መልዕክት አለ። ይህም የሚያሳየው ያ መልዕክት እጅግ ወሳኝና ከባድ መሆኑን ነው። ለዚያ መልዕክት ጂብሪል አልተላከም። ነቢዩ ራሣቸው ናቸው መልዕክቱን እንዲቀበሉ ወደ ሰማይ የተጠሩት። ያ መልዕክትና ትዕዛዝ ሶላት ነበር። የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) መጀመርያ ላይ የሶላትን ግዴታነት ከአምላካቸው ሲቀበሉ በቀን ውስጥ ሀምሳ ሶላት እንዲሰገዱ ነበር። ከነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ.) በተሠጣቸው ምክር አላህ እንዲያቀልላቸው በተደጋጋሚ ከተማጸኑ በኋላ ወደ አምስት እንዲወርድላቸው ተደረገ። ሶላቶቹ አምስት ቢሆኑም ምንዳቸው ግን ሀምሳ ነው። ምስጋና ለአላህ ይገባው።

ሙስሊም ምሑራን በዚሁ ዙርያ ሀሳባቸውን ሲገልጹ ሶላት ከሀምሳ ወደ አምስት እንዲወርድ መደረጉ ሆነ ተብሎ ነው። ሶላት በኛ ሕይወት ውስጥ ያላትን እውነተኛ ቦታ ለማስተማር ነው። ለምሳሌ በቀን ሀምሳ ጊዜ ሰገድን እንበል። ከሶላት ውጭ ሌላ የምንሠራው ነገር ሊኖር ይችላልን? አዎን አንችልም። ይኸው ነጥብ ነው የተፈለገው። የመፈጠራችን ዋና ዓላማ በተገቢው ሁኔታ ከማሳየት በላይ ምን አለ። ሶላት ትክክለኛዋ ሕይወታችን ናት። በሷ እንቅስቃሴ ቀናችንን እንሞላባታለን።

ዛሬ ላይ ግን ብዙዎቻችን ተቃራኒውን እየኖርን ያለን ነው የምንመስለው። ሶላትን የምንሰግደው በቂ ጊዜ ሲኖረን ብቻ ነው። ሕይወታችን በሶላት ዙርያ የሚያጠነጥን አይደለም። ሶላት ናት በኛ ሕይወት ዙርያ ማጠንጠን ያለባት። እኛ ግን ትኩረት ነፈግናት። ለትምህርት ከፍል ከገባን ከላስ ስንጨርስ ነው የምንሰግደው። የገበያ አዳራሽ ውጥ ከገባን ግብይታችንን ነው የምናስቀድመው። ኳስ ለመመልከት ብለን የኛን የሕይወት ዋና ዓላማ ወደኋላ የምንገፋ ከሆነ ከባድ ስህተት እየሠራን እንደሆነ ልናውቅ ይገባል።

ይህ እንግዲህ በሚሰግዱ ሰዎች ዘንድ የሚታይ መጥፎ ባህሪ ነው። በሌላ በኩል የመፈጠራቸው ዓላማ የሆነችውን ሶላትን ከናካቴው የተው ደግሞ አሉ። ሶላትን ከመተው አንጻር ብዙዎቻችን ያላስተዋልነው አንድ ነገር አለ። ይኸውም :- ለምሳሌ አንድ ሰው ዝሙትን ያህል ትልቅ ወንጀል ቢሠራ ከእስልምና ወጥቷል የሚል ዓሊም የለም። እንዲሁም መስረቅ፣ መጠጣት፣ ማጨስና የመሣሉትንም እንዲሁ ከእስልምና ያስወጣል ያለ የለም። ሌላው ቀርቶ መግደል ጭምር ሙስሊምን ከእምነቱ ያስወጣዋል ያለ የለም። ግና በሶላት ጉዳይ አንዳንድ ዑለሞች ሶላትን የተወ ሰው ሙስሊም አይደለም ብለዋል። ይህንንም ሲሉ ተከታዩን ሐዲሥ በመመርኮዝ ነው።

"በኛ እና በነርሱ መካከል ያለው ኪዳን ሶላት ነው። ሶላትን የተወ በአላህ ከዷል።"
(ኢማም አሕመድ እንደዘገቡት)

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን ያሉት ሶላትን መተው እጅግ መጥፎ ድርጊት በመሆኑ ነው። ለአፍታ ያህል ከጀነት የተባረረው ሸይጣን ምን እንዳጠፋ እንመርምር እስቲ። በአላህ አለማመን አልነበረም ችግሩ። ለአደም አልሰግድም ነበር ያለው። አንዲት ሱጁድ እንዲያደርግ ሲታዘዝ አሻፈረኝ አለ። አንዲት ብቻ። ብዙ ሱጁዶችን እንቢ ያለ ሰው ዕጣ ፈንታው ምን ሊሆን እንደሚችል አናስብ።

የዚህ ዓይነቱ እንቢተኝነት ምን ያህል ከባድ ወንጀል እንደሆነ እናስተውል። እኛ ደግሞ የሶላትን ጉዳይ እንዴት ቀለል አድርገን እንደተመለከትን ልብ እንበል። በፍርዱ ቀን መጀመርያ ላይ የምንጠየቀው ስለ ሶላት ነው። ታዲያ እኛ ለምንድነው ወደኋላ ያስቀረናት? የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) "በትንሳኤ ቀን ከሥራው መካከል አንድ ባርያ መጀመርያ ላይ የሚመረመረው በሶላት ጉዳይ ነው። ሶላቱ መልካም ከሆነች በርግጥም ተሳካለት፤ የተመኘውንም አገኘ። እሷ ከተበላሸች በርግጥም ባዶ ሆነ፤ ከሰረ።" ብለዋል።
(ቲርሚዚ ዘግበውታል።)

የቂያማ ቀን የጀነት ሰዎች እሣት የገቡትን ሰዎች ይጠይቃሉ። ለምን እሣት እንደገቡ። ቁርአን የመጀመርያ ምላሻቸው ምን እንደሆነ ከምልልሳቸው ይነግረናል።

﴿ مَا سَلَكَكُمْ فِي سَقَرَ ﴿٤٢﴾ قَالُوا لَمْ نَكُ مِنَ الْمُصَلِّينَ ﴾

«(ይሲችሞልም) “በሰቀር ውስጥ ምን አገባችሁ?” (አነርሱም) ይሳሱ “ከሰጋጆች አልነበርንም።» (አል-ሙደሣር : 42-43)

ታዲያ ከኛ መካከል ስንቶቻችን ነን ነገ “ከሰጋጆች አልነበርንም፤ ወይም ደግሞ በጊዜዋ ውስጥ ሶላትን የምንሰግድ አይደለንም፤ ወይም ደግሞ ሶላትን በሕይወታችን ውስጥ ከሁሉም ነገር አስቀድመን የምንሰግድ አይደለንም፤” ልንል የምንችል? ይህ ሊያሳስበን ይገባል።

ለምንድነው ከላስ ካለን፣ ወይም ሥራ ከሆንን ሱብሒ ሰዓት መድረሱን እያየን የምንተኛው? ለግዴታ ሶላታችን ከተሠጠን ጊዜ እየቀነስን የምንጠቀምው ለምንድነው? በርግጥ ጥያቄው ተራ ነገር ይመስላል። ግና በሶላት ጉዳይ ምን ያህል ቸልተኛ እንደሆንን ማሳያ ነው። መጨነቃችን ለምድራዊ ጉዳዮች ነው። የሆነ ፈተና ሲኖርብን ሰዓቱ እንዳያልፍብን እንቅልፍም አይወስደንም። በጊዜ ነው አስቀድመን ወደ መፈተኛ ቦታ የምንሄደው። ምክንያቱም ሊከተል የሚችለው ነገር ጥሩ እንዳልሆነ ስለምናውቅ ነው። ሶላትም የመተው ጣጣው ግን ከዚህ የበለጠ እጅግ ከባድ ነው።

ብዙ ሰዎች በሥራም ሆነ በትምህርት ቤት አሊያም ከቤት ሲወጡ ለመስገድ ጊዜ አናገኝም ይላሉ። ግና ከሶላት ውጭ ላሉ ለተለያዩ ነገሮች ጊዜ አያጡም። ነገሩ እኛ ራሣችንን እንደምናታልለው አይደለም። በደንብ ብናስብበት ኖሮ መፍትሔ አናጣለትም ነበር። ግና ይህን ማስተዋል አልቻልንም። ከነፍሣችን ይልቅ ለአካላችን ምግብ ነው ብዙ የምንጨነቀው። ምግብ ባንመገብ እንሞታለን ብለን እናስባለን። ነፍሣችን ስትራብ ግን ዝም ብለን እንመለከታታለን። ሶላት አንዷ የነፍስ ምግብ ናት። እኛ ያስራብናትና የረሳናት ነፍስ ተሻጋሪ እና በቀጣዩ ዓለም ከኛ ጋር የምትሆን ናት። እኛ የምንጨነቅለት ገላ ግን ፈራሽ እና ጊዜያዊ መሆኑን ልናውቅ ይገባል።

CamScanner